# ተስፋዬ ገብረአብ እስከአሁን የት ነበርክ ?

ተስፋዬ ገብረአብ ይባላል። የተወለደዉ ደብረዘይት (ቢሾፍቱ) ሲሆን አባትና እናቱ መንደፈራ ተጋብተዉ ይኖሩ የነበሩ የኤርትራ ተወላጆች ናቸዉ። ለሃያ ቀናት የደርግ ወታደር ሆኖ ደብረታቦር በወያኔ ተማረከ። ወዲያዉ በወያኔ ዉስጥ ትልቅ ቦታ ተሰቶት የወያኔ ቀንደኛ የፕሮፖጋንዳ ሃላፊ ሆነ። ወያኔ ስልጣን ሲጨብጥ በሃያ ምናምን አመቱ የኢትዮጵያ ፕሬስ መምሪያ ሃላፊነትን ጨበጠ። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፣ አዲስ ዘመን፣ ኢትዮጵያያን ሄራልድ የመሳሰሉት በርሱ ስር ወደቁ ማለት ነዉ።

አሁን ነዋሪነቱ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ ሲሆን በቅርቡ «የጋዜጠኛዉ ማስታወሻ» በሚል በግሩም አማርኛ ነዉ የተጻፈ አንድ መጽሃፍ ጽፈዋል።

ይህ ሰዉ እኛ የምንጽፈዉን ቢያነብ በርግጥ አማርኛዉን ቀለዱበት ብሎ እንደሚታዘበን አስባለሁ። መጽሐፉን አንብቤ ዝም ብል ደስ ባለኝ ነበር፤ ነገር ግን በመጽሃፉ ከያዝኳቸዉ አንዳንድ ነጥቦች በመነሳት በርካታ ጥያቄዎች በአይምሮዬ ስለተጫሩ ከናንተ ጋር አብሬ ጥያቄዎቹን ለመመለስ ፈለኩኝ። ይችንም መጣጥፍ አቀረብኩ።

መጽሃፉ በአንዳንድ ድህረ ገጾችንና የፖለቲካ ድርጅቶች የተጋነነለት እንደመሆኑ ትምህርት ሰጪና ጠቃሚ ሃሳቦችን አገኛለሁ ብዬ ጠብቄ ነበር። በተለይም ደራሲዉ በመጽሃፉ እንደሚናገረዉ በወያኔ ዉስጥ እጅግ በጣም ትልቅ ሰዉ እንደነበረዉ አድርጎ ነዉ ያቀረበዉ። አንድ ቦታ «በዚያን ወቅት የደህንነቱም ሆነ አባ ዱላ ገመዳ የሚመራዉ የወታደራዊ ደህንነት ሰነዶች ለኔ በራቸዉ ክፍት ነበር። የፈለኩትን ሰነድ የመመርመርና ወደቤት ተዉሼ የመዉሰድ ልዩ ፈቃድ ተሰቶኛል» ሲልም ጽፈዋል።

እንግዲህ ይህን ያህል በሩ የተከፈተለት ሰዉ ሆነ በመጽሃፉ ያቀረበልን አብዛኞቻችን ከምናዉቀዉ ዉጭ ይሄ ነዉ የሚባል ቁም ነገር የለም። አንባቢያንን ለማጭበርበር ከእዉነት የራቀ ዉሸት የሞሉባቸዉ የተጻፉ ታሪኮችን እናያለን።

ለምሳሌ ሁለቱን ልጥቀስ። ጸሃፊዉ የቀድሞ የመአእድ ሊቀመንበር ስለነበሩት ደጃዝማች ነቃ ጥበብ ይናገራል። ምናልባት ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ እራስቸዉን መመከት አይችሉም ብሎ ይሆናል ስማቸዉን የሚያጠፉት። ጸሃፊዉ ቀኛዝማች ነቅዓጥበብና የወያኔ የደህንነት ሃላፊ የነበረዉ ክንፈ ወዳጆች እንደሆኑ አድርጎ ያቀርባል። በጣም የሚያስቀዉና የሚያሳፍረዉ ቀኛዝማች ነቅዓጥበብ በሕዝብ ድጋፍ እንዲያገኙ «እንደዉ አንድ ሳምንት እስረኝ» ብለዉ ክንፈን እንደጠየቁ በመጽሃፉ እናነባለን።

እንግዲህ አስቡት … ሰዉዬዉ እንደፈለገ ክንፈ ጽ/ቤት ገብቶ የፈለገዉን መረጃ ማግኘት ስለሚችል ክንፈና ደጃዝማች የተነጋገሩትን ሚስጥር ማወቅ ቻለ። ልብ በሉ ክንፈም ደጃዝማችም አሁን በሕይወት የሉም።

እዚህ ላይ ሰዉዬዉ ለቀድሞ መኢአድ ደጋፊዎችና አመራር አባላት ያለዉን ንቀት ያሳየል። (በነገራችን ላይ ይህ ሰዉ የደህነንት መረጃ በሰፊዉ ተከፍቶለት ስለ ፕሮፌሰር አሥራት ያንጠባጠበዉ አንዲት ጠብታ የለም። )

እንደ ሁለተኛ ምሳሌ የማቀርበዉ የጄኔራል ኃየሎም አሟሟት ላይ ጸሃፊዉ የዘገበዉን ነዉ። ጄነራል ኃየሎምን የገደለዉን ሰዉ እርሱ ብቻ እንዳነጋገረ ጽፎልናል። ማሪዋና ወስዶ በጅልነት ገዳዩ ኃየሎምን እንደገደለ እንጂ ሌላ ምክንያት እንደሌለ አስረግጦ ይነግረናል። ይሄንንም ዉሸት እንድናምንለት ኀየሎምን እስኪገድል ድረስ ማሪዋና ገዳዩን እንዴት ማንደንዘዝ እንደቻለ ለማወቅ ጸሃፊዉ እራሱ ማሪዋና እንደተጠቀመና ጅላጅል እንደሆነም ጠቅሷል። (የጸሃፊዉን አባባል ልጠቀምና)

በ1991 ሻቢያ ኢትዮጵያዉያንን የጥርሳቸዉን ወርቅ እያወለቀ እንዳባረረና ከኤርትራም በጉልበት የተፈናቀሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲት ግንብ፣ በአራዳ ጊዮርግስ ቅጥር ግቢ ዙርያና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ዳር የላስቲክ ቤት ሰርተዉ ይኖሩ እንደነበረ ሁላችንም የምናስታዉሰዉ ነዉ። (በነገራችን ላይ ይህ አሳዛኝ ክስተት በዚህ መጽሐፍ ላይ አልተጠቀሰም)።

በዚያን ወቅት ኢንዲያን ኦሽን የተሰኘዉ ጋዜጣ ላይ ስዩ አብራሃና ኃየሎም አርዓያ በሻቢያ በጣም ከመናደዳቸዉ የተነሳ ሻቢያን መምታት ይፈልጉ እንደነበረ  ተጽፎ ማንበቤ ትዝ ይለኛል።

በጣም የምቀርባቸዉ ትግሬ ወዳጆች ነበሩኝ። የወያኔ ሻለቃ አጎት ነበራቸዉ። ገብረ መድህን ይባላል። እነርሱ ገሬ ነዉ የሚሉት። (ገብረ መድህን የሚለዉን ስም በጣም ነዉ የምወደዉ። በቴስታ የታወቀዉ የጊይርጊስና የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ገብረ መድህን የሚባል ስለነበረ) ታዲያ ያኔ ይህ የወያኔ ሻለቃ በኢንዲያን ኦሽን ያነበብኩትን አልካደም። ስዬና ኃየሎም ኢትዮጵያ ባህር አልባ መሆኗ እንዳላስደሰታቸዉና የኤርትራ መገንጠል እንደሚያበሳጫቸዉ በግልጽ አጫዉቶኝ ነበር።

እነዚህ ሁለት ሰዎች (ስዬና ኃየሎም) በሻቢያ ዘንድ ከመጀመሪያዉኑ የሚጠሉ ግለሰቦች ናቸዉ። ኢሳያስ ከየመን ጋር በሃኒሽ ደሴቶች የይገባኛል ጥያቄ ጦር ሲሰብቅ፣ መለስ ዜናዊ ደግሞ አሰብ ላይ የነበረው የኢትዮጵያ የአየር መከላከያ ሲስተም (Air Defense System) ለኤርትራ አገልግሎት እንዲውልና የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይልም የኤርትራን ሰራዊትን እንዲያግዝ ቀጭን ትእዛዝ በሰጡበት ወቅት፣ ኃየሎም አልነበረም እንዴ “ሻቢያ ባበደ ቁጥር ለምን የኢትዮጵያ ወታደር የጦርነት ሰለባ ይሆናል?” ብሎ በብርቱ የተቃወመ?

ኃየሎም የተገደለዉ በተቀነባበረ የኢሳያስና የመለስ ሥራ እንደሆነ ማንም እያወቀዉ ይህ ጸሃፊ የኃየሎምን መገደል በአንድ በማሪዋና በሰከረ “ኤርትራዊ ጅል” እንደተፈጸመ አድርጎ መደምደሙ እራሱ ጸሃፊዉን ትዝብት ዉስጥ አይከተዉምን ?

አብዛኞቻችን እንደምናዉቀዉ የባድመ ጦርነት እስኪነሳ ድረስ ሻቢያና ወያኔ እጅና ጓንት ነበሩ። እንደዉም ኤርትራ ቡና ለዉጭ ገበያ ታቀርብ እንደነበረ የሚታወስ ነዉ። አንድ ወቅት ጤፉና እህሉ ትግራይን እያቋረጠ ወደ አሥመራ ብቻ ይሄድ ስለነበረ የትግራይ ምክትል አስተዳዳሪ የነበረችዉ ወ/ሮ አረጋሽ ትሬንታ ኳትሮዎቹን እንዲቆሙ አዛ እንደነበረ ሲወራ አስታዉሳለሁ። ለ7፣ 8 አመት ያህል ሻቢያ በኢትዮጵያ እንደፈለገ ያደርግ የነበረበትም ጊዜ ነበር። እንደዉም የኢትዮጵያ መሪ ተደርገዉ የሚታዩት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ እንደነበሩ የሚታወስ ነዉ።

እንግዲህ ይህ ጸሃፊ ሻቢያ በኢትዮጵያ ዉስጥ ያደረገዉን አንዲት ቅንጥት ያህል አልጻፈም። የተላይዩ መረጃዎች ይደርሱት ከነበረና የዉትድርና የደህንነት ሰነዶችን በሙሉ እንዲያነብ ከተፈቀደለት ታዲያ ኤርትራዉያኖቹ የሰሩትን ሥራ ምነዉ አይጠቀስም? በመጽሃፉ ላይ የምናየዉ የሻቢያ ጀግንነት ነዉ። ሰዉዬዉ እገሌ ነገረኝ እያለ የሚጽፋቸዉ ብዙ ተራ ወሬዎች አሉ። አንዴ ለሃይ ቀናት የኢትዮጵያ ወታደር የነበረ ጊዜ አንድ የጦር አዛዥ ነገረኝ ብሎ « በከባድ መሳሪያ የበላይነት አላቸዉ። ተኩሰዉ (መድፉን ማለት ነዉ) የምሳ ሳህን ላይ ቁጭ ያደርጉልሃል» (ገጽ 42) ሲል የሻቢያን ጀግንነት ሲያጎላ ነዉ የምናየዉ።

ጸሃፊዉ ስለ ወያኔ ክፍፍል በሰፊዉ ዘግቧል። ነገር ግን የብዕር ኢላማዉን ያነጣጠረዉ በነአቶ ስዬ አብርሃ ቡድን ላይ ነዉ። (የነስዬ ቡድን አቶ ገብሩ አሥራት የቀድሞ የትግራይ አስተዳዳሪ፣ አቶ ተወለደማሪያም የቀድሞ የወያኔ ምክትል ሊቀመንበርን ያቀፈ ቡድን ነዉ).

«እነ ተወልደ ሉዓላዊነትን ከማስከበር ባሻገር ሌላ አጀንዳ እንደነበራቸዉ ለመረዳት በዙሪያዉ ለነበርነዉ ሁሉ አዳጋች አልነበረም። የአንጃዉ አባላት ሻዕቢያን ከሚጠሉት ባላነሰ ሁኔታ በኤርትራ ሕዝብ ላይ የመረረ ጥላቻ ነበረቸዉ» ይላል ጸሃፊዉ በገጽ 184.

በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት የከፈተዉ ሻቢያ ነዉ። እነ አቶ ስዬ ከመጀመሪያዉኑ ሲቃወሙ ሻቢያ የልብ ልብ እንዲያገኝ ያደረጉት ጸሃፊዉ ብዙ የማይተቻቸዉ እነ መለስ ዜናዊ ናቸዉ። ደራሲዉ አቶ ስብሀት ነጋን አቶ ስዩም መስፍንን ተችቶ የጻፈበት ቦታ የለም። አቶ መለስ ዜናዊንም የሚቃወም እየመሰለ ማሳረጊያው ላይ "ብልህ መሪ" ሲል ያወድሳቸዋል። የሻቢያን ጥቃት በመመከትና መልሶ ድምጥማጡን በማጥፋት አስመራ ደጃፍ መድረስ የተቻለዉ በነስዬ መሪነት ነዉ። የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም በጎዳ መልኩ ከዉጫሌ ዉል የማይተናነስ የክህደት ሥራ የሰሩት እነ አቶ መለስ እንጂ እነ አቶ ስዬ አብርሃ አይደሉም። ባድመ ለኢትዮጵያ ሳይሰጥ ባደመ ለኢትዮጵያ ተሰጧል ብለዉ ሕዝቡን በዉሸት ጮቤ ያስረገጡት እነ አቶ መለስ ናቸዉ። ታዲያ ይሄ ሁሉ ታሪካዊና አበይት የሆኑ ዘገባዎች ደራሲዉ ምነዉ ዘነጋቸዉ ?

በነአቶ መለስና በነስዬ መካከል የተፈጠረዉ ችግር በዋናነት የባህር በር ጉዳይ መሆኑ እየታወቀ ደራሲዉ ምን ጭብጥ በእጁ ይዞ ነዉ እነስዬ የኤርትራን ህዝብ እንደሚጠሉ የሚጽፈዉ ?

ያ ብቻ አይደለም ሰዉዬዉ ፕሪቶሪያ ተቀምጦ አሁን ስለሚደረገዉ ትግልም ሃሳብ ሊሰጠን ይፈልጋል። «እነ ተወልደ አረና የሚል ስም ይዘዉ ተመልሰዋል። የኤርትራ ስምም ከዘመን ዘመን እንደ ጨዉ በርበሬ የፖለቲካ ማጣፈጫ እንደሆነ ቀጥሏል» ይለናል ገጽ 193 ላይ በአረና ትግራይ ላይ ያለዉን ችግር ሲነግረን። በገጽ 197 ስለነተወልደ መናገሩን ሲቀጠል «ከመለስ ተወልደ ይሻለናል ነዉ ጠባቸዉ እንጂ ብርቱካን ሚደቅሳን ስልጣን ላይ ማየት ከቶ አይሹም» ይለናል። (አቶ ተወልደ የአረና አባል መሆናቸዉን አላዉቅም። ደራሲዉ ከየት እንዳመጣዉ ቢነግረን ጥሩ ነበር)

ልብ በሉ እንግዲህ እዚህ ላይ። ጸሃፊዉ የባጥ የቆጡን ሲደበላልቅ ይታያል። ብርቱካን ሚድቅሳ እዚህ ላይ ምን ልታደርግ እንደገባች አይገባኝም። የአራና ትግራይን የፖለቲካ ፕሮግራም አንብቤዋለሁ። ስለኤርትራ ብዙ የተናገሩት ነገር የለም። ያሉት ኢትዮጵያ የባህር ወደብ እንደሚያስፈልጋት ነዉ። **አሰብ በሕግ በሰላም የኢትዮጵያ እንድትሆን መታገልና መከራከር አለብን ነዉ የሚሉት።** ይህ አሰብን በተመለከተ ያላቸዉ አቋም የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አሁን ደግሞ የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ አቋም ነዉ። ይህ አቋም የእያንዳንዱ ኢትዮጵያን የሚወድ ሰዉ አቋም ነዉ።

አረና ትግራይ ሕወሃትን ተክተዉ እነርሱ ስልጣን ላይ ለመዉጣት ሲንቀሳቀሱ አናይም። ለትግራይ ብቻ ሲቆሙ አናይም። ይልቅስ በሌሎች ኢትዮጵያዉያን ጋር መተባበሩ ብቸኛ መፍትሄ ነዉ በሚል «መድረክ» በሚባለዉ አካል ዉስጥ ታቅፈዉ እየሰሩ ናቸዉ።

«ብርቱካን ሚደቅሳን ስልጣን ላይ ማየት አይፈልጉም» ለተባለዉ ደራሲዉ መረጃ ይጎድለዋል እንጂ ብርቱካን ሚደቅሳና የአንድነት ፓርቲ በአረና ትግራይ አመራር አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም በትግራይ ህዝብ የተወደዱ ናቸዉ። በአረናና በአንድነት ፓርቲ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ፌድራሊስት ፓርቲ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያ ኃየሎች ህብረት፣ የሶማሌ ዲሞክራሲያዊ ቅንጅት ... ሁሉም በመከባበር በጋራ ለአንዲት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሰላምዊ በሆነ መንገድ እየሰሩ ናቸዉ። ደራሲዉ ብርቱካን ሚደቅሳን ከአረና ለማጣላት ከሆነ ተልእኮዉ የቤት ሥራዉን በደንብ የሰራ አይመስለኝም። ደራሲዉ አረና ትግራይ ሆነ የአረና አባል ያልሆኑት አቶ ስዬ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንዲፈቱ በግንባር ቀደም እየታገሉ ያሉ ወገኖች ናቸዉ።

ደራሲዉ አንዳንድ የሚታወቁ ስሞችንም ጠቅሰዋል። ለአቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌና ለአቶ ያሬድ ጥበቡ ቀና አስተያየት እንዳለዉ አነባለሁ። ኢትዮጵያ ሪቪዉንም ያደንቃል። ስለኦሮሞ ነጻ አዉጪ ግንባር በጥሩነት ከመናገር ዉጭ ሌላ ነገር አልወጣዉም። የ“ኦሮሞ ህዝብ እንደተበደለ” በሰፊዉ ጽፈዋል። በርግጥ የ”ኦሮሞ” ህዝብ እንደሌላዉ ኢትዮጵያዊ  ግፍ ደርሶበታል። የአንዱን ግፍ እያጎሉ ማሳየት እዉነት ቢሆንም አላማዉ ከፋፋይ ነዉ። ደራሲዉ የመከፋፈል ሥራ ነዉ ለምሥራት የሞከረዉ።

“አማራውን ኦሮሞው» በትግሬው ላይ እንዲነሱ የሚያደርግ መርዛማ ፕሮፖጋንዳ ለመርጨት የሚፈልግ ይመስላል። በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲኖር የሚታገሉ የትግራይ ወገኖቻችን ሰይጣናዊ በሆነ መልኩ ያቀርባቸዋል። ሻቢያ እንዲነካ አይፈልግም። ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘቷን ነገር ያጣጥላል። በኢትዮጵያ ትግል ትልቅ አስተዋጾ ያደረጉ ጠንካራ የዲሞክራሲ ታጋዮች እንደ አቶ ሙሉጌታ ሉሌና እንደ አቶ አብርሃ በላይ አይነቶችን ይተቻል።

ስለ አቶ ሙሉጌታ ሉሌና ስለ ኢትዮሚድያ አዘጋጅ አቶ አብርሃ በላይ አስተዋጽኦ የኢትዮጵያ ህዝብ ነጋሪ አያስፈልገዉም። ሥራቸው ይናገራል። አቶ አብርሃ በላይ ቀን በቀን ከገዢው ፓርቲ ጋር እስከአሁን የሚታገሉ ቆራጥ ኢትዮጵያዊ ናቸው። እርሳቸው የሚያዘጋጁት የኢትዮሜዲያ ድህረገጽ በአሁን ወቅት ኢትዮጵያ ዉስጥ የታገደ ድህረገጽ ነዉ። አቶ ሙሉጌታ ሉሌ የጦቢያ ዋና አዘጋጅ የነበሩ ከዚያም የኢትዮጵያውያን ቴሌቭዥን ኔትዎርክ ዋና ሃላፊ ሆነው ስንት ስራ ሲሰሩ የነበሩ ታላቅ የሜዲያ ባለሞያ ናቸው።

ታዲያ ለአመታት የወያኔ/ሻቢያ ፖሮፖጋንዳን በአዲስ ዘመን በመሳሰሉ ሲረጨን የነበረ፣ በስደት አለም አንዴ ሲያትል አንዴ ደርባን ሲዞር ዉብ የመጻፍ ችሎታዉን ተጠቅሞ በዲሞክራሲና በአገር አንድነት ዙሪያ አንዲት ጽሁፍ ያልወረወረና ላለፉት ሶስት አመት ኢትዮጵያዊያን ከወያኔ ጋር ሲታገሉ ድምጹን ያጠፉ ሰዉ በምን ሞራል ኦቶሪቲ ነዉ እነዚህ ሰዎች የሚያንቋሽሸዉ ?

ያ ብቻ አይደለም። ቅንጅት፣ አንድነት ፣ ሕብረት እንዲሁም በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲኖር እራስቸዉን ሰዉተዉ ፊት ለፊት ሰላምዊ ትግል እየተጋሉ ያሉትን ወገኖቻችንም ያዋረደ ሰዉ ነዉ። የሚያደርጉትን ትግል በመጽሃፉ ያንቋሽሻል። « በሰላማዊ ትግል ተስፋ ያልቆረጡ ወገኖች ትግላቸዉን ቀጥለዋል። የሰላምዊ ትግል ዉጤት በተደጋጋሚ የሕዝን የነጻነት ጥያቄ አኮላሽቶታል» ይለናል በግጽ 399።

ላለፉት አሥራ ስምንት አመታት ቢያንስም ቢበዛም በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ፣ ወይኔን ሲታገሉና ሲያጋልጡ የኖሩት በሰላማዊ ትግል የሚታገሉ ኃይላት ናቸዉ። ታዲያ እንዲሁ በባዶ ፣ ሌላ የሚታይና የሚጨበጥ አማራጭ ሳያሳዩን፣ እነዚህ በሰላማዊ ትግል የሚታገሉትን ኃይላት ትግላችሁን አቁሙ ማለት መለስና በረከትን ተዝናንታቹህ ሕዝቡን እያፈናቹህ ኑሩ እንደማለት አይቆጠረምን? ከላይ እንደዘረዘርኩት የዚህን መጽሃፍ ይዘት ስናየዉ፣ ዓላማዉ ኢትዮጵያን የሚጠቀም ሳይሆን ዉስጡ መርዝ የተሞላ፣ በሻብያ የተቀነባበረ መጽሃፍ እንደሆነ መደምደሙ ያስቸግረናልን ? በኢትዮጵያ የሚደረገዉ ሰላማዊ ትግል አክትሞ በሻቢያ ላይ ጥገኛ የሆነ አስመራ ማእከሉ ያደረገ ትግል እንዲደረግ የሚገፉፋ መጽሃፍ አይደለምን?

ይህ ጸሃፊ ያለምን ጥርጥር የሻቢያ ቅጥረኛ እንደሆነ ከጽሁፉ ለመረዳት ይቻላል። መጽሐፉን ያሳተመዉ የታተመዉ መጽሐፍ ደግሞ በተደራጀ ሁኔታ እንዲሸጥ የሚያደርግ ከበስተጓላ የተደራጀ ኃይል እንዳለ ለመገምት አያቅትም። ይህም ኃያል

**ሻቢያ ነዉ። ለዚህም ነዉ ህዝባችንን ከዉዥንብር ለማዳን ይችን ጽሁፍ ያቀረብኩት።**

**እግዚአብሄር ያክብርልኝ !**

**አበበ ቀልቤሳ**
kelbessa@yahoo.com